## ሳምንታዊ ዜና (ጥቅምት 29 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**የአልሸባብ አጥፍቶ ጠፊዎች አዲስ አበባ ገቡ ተብሎ ከተማዋ በፍተሻ እየተናጠር ነው፣ የቦሌ አውሮፕላን ማሪፊያና ስታዲዮምም ጥብቅ ፍተሻ ተደረገባቸው፣ የአውሮፕላን በረራ ለ8 ሰአታት ዘገዬ፣ በኦጋዴን አልሻባብ እና ኦብነግ በወያኔ ጦር ላይ ጥቃት አደረሱ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የንግድ ስራ ተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ አሰሙ፣ የእውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን የፍርድ ቤት ውሎ በ7 ደቂቃ ቀጠሮ ለወር ተቀጠረ፣ የእንቢልታ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ 2 ሺህ ብር ተቀጣች »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ....................................**

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አጥፍቶ ጠፊዎች ገብተዋል በሚል ወያኔ ከፍተኛ ጥበቃ እና ፍተሻ እያደረገ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::የአልሻባብ አጥፍቶ ጠፊዎች ከነ ሙሉ ትጥቃቸው አዲስ አበባ ጥቃት ለመሰንዘር ገብተዋል በሚል ከጥቅምት 23 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ ጥብቅ ፍተሻ እየተደረገ መሆኑ ታውቁዋል::

እሁድ ጥቅምት 23 ቀን 2001 ዓ. ም. በአዲስ አበባ ስታዲየም የቅዱስ ጊዮርጊስና የኢትዮጵያ ቡና እግር ኩዋስ የዋንጫ ጨዋታ ለመመልከት የተገኙት ከ30 ሺህ ህዝብ በላይ በሙሉ ግልገል ሱሪ ሳይቀር ፍተሻ እየተደረገ ወደ ስታዲየሙ የገቡ ሲሆን ፣ ሊፒስቲክ ፣ ቻፒስቲክ ፣ የጥፍር ቀለም ሳይቀር እየተነጠቀ የተጣለ ከመሆኑም ባሻገር ሞባይል ቀፎ እየተከፈተ ጥብቅ ፍተሻ መደረጉ ታውቆዋል::

የወያኔ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት ግብረ ሀይል ደረሰው በተባለው ጥቆማ መሰረት በአዲስ አበባ ስታዲየም እሁድ እለት የተጀመረው ጥብቅ ፍተሻ ሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ. ም.ከሌሊቱ 6 ሰዓት እስከ ማግስቱ ከጡዋቱ 4 ሰዓት ድረስ እጅግ የጠበቀ ፍተሻ በቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የተደረገ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

የቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሠራተኞች ሳይቀር ጥብቅ ፍተሻ የተደረገባቸው ሲሆን፤ በዚሁ እለት ከሌሊቱ 6 ሰዓት ጀምሮ በረራ ለ8 ሰዓታት ያህል ተቋርጦ እንደነበረ ያስታወሰው ዘገባው የአልሻባብ አጥፍቶ ጠፊዎች የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያን ለማጥቃት ካሰቡት ውስጥ አንዱ ነው በማለት ፍተሻና ብርበራ የተደረገ ሲሆን በተለይ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡም ሆነ ወደ ውጭ ሀገር ለመብረር የተዘጋጁ ፓይለቶች ጭምር ጥብቅ ፍተሻ የተደረገባቸው መሆኑን ዘገባው ገልፆዋል::

በዕለቱ በተደረገው ፍተሻ ምክንያት የበረራ መስመሮች ሁሉ ላልተወሰነ ሰዓታት ተቋርጦ እንደነበር የገለፀው ዘገባው በርካታ መንገደኞችም ከጉዞዋቸው ለመዘግየት እንደተገደዱም ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

የአልሻባብን ተዋጊ ኃይል አከርካሪውን መትተናል ፤ከእንግዲህ የሚያስፈራ ነገር የለም እያለ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቢፎክርም ዛሬ ድንገት ጥቃት ሊያደርሱብን መሆኑን መረጃ ደረሰን በማለት ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ማለታቸው በእቅድና በፕሮግራም የማይመሩ ፤ከሚሰሩት ይልቅ የሚያወሩት የሚበልጥ ውሸታሞች መሆናቸውን ያሳየ ነው ያሉት አንድ የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሠራተኛ ከዚህ ቀደም ከአንድ ወር በፊት የአልሻባብ ጥቃት አድራሾች ወደ ውጭ የሚወጡና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የወያኔ ባለስልጣናት ላይ በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ጥቃት ሊያደርሱ ነው በሚል በመደናገጥ የደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣናት ለብቻቸው ጥበቃና ክትትል ሲያደርጉ እንደነበረም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

ሳይሉዋቸው ሱማሊያ ምድር ገብተው ወታደሮቻቸውን ያስጨረሱት እነ መለስ ዜናዊ የአልሻባብ ፈረስ ከሞቃዲሾ ደንብሮ አዲስ አበባ እንዳይገባ የተሳፈሩትን ማውረድ ግድ ስለሚል እንዲወርዱ አድርገናል በማለት በዚሁ ዓመት መባቻ ላይ የወያኔ ፓርላማ በተከፈተ በሳምንቱ መለስ ዜናዊ የገለፀ ቢሆንም ይህንን በገለፀ ጥቂት ቀናት ውስጥ የአልሻባብ ታጣቂዎች አዲስ አበባ ገቡ በማለት ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ እያሉ ተወጥረው መገኘታቸው አሳዛኝና አሳፋሪ ብቃት የሌላቸው መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው ሲሉ እኚሁ የድርጅቱ ሠራተኛ ገልፀዋል።

ሰኞ ዕለት የተጀመረው ጥብቅ ፍተሻ ለ10 ሰዓታት ያህል የፈጀ ከመሆኑም በላይ አውሮፕላን ማረፊያው ባለጎማ ብረት ለበስ ከባድ መሳሪያ ዙሪያውን ታጥሮ ጥበቃ እየተደረገ እና እንደ አሜሪካ ኤምባሲ በኮንክሪት መከላከያ መታጠሩን ዘገባው ገልፆ የወያኔ ባለስልጣናት ስጋታቸው ከማየሉ የተነሳ አየር ማረፊያውን ለመጠበቅ የተመደበው አንድ ሻለቃ የፌዴራል ፖሊስ ከሌላው ጋር እንዳይገናኝ ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገበት መሆኑንም ጨምሮ የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።

ይህንኑ ተከትሎ በአዲስ አበባ ከወትሮው በተለየ መልኩ በፌዴራል ፖሊስ እና ጀሌ በሆኑ የአዲስ አበባ ፖሊሶች ከመቸውም ጊዜ በላይ ጥብቅ ጥበቃ እየተደረገ ሲሆን፣ በተሽከርካሪ ላይ በተጠመደ መትረየስ ጭምር የተጠናከረ የፓትሮል ጥበቃ እየተካሔደ መሆኑንም ከዓይን እማኞች ገለፃ ለመረዳት እንደተቻለ ዘገባው አስረድቷል።

ረቡዕ ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ. ም. አራት ኪሎ ቤተ መንግስት አካባቢ እጅግ ከወትሮው የተለየ መጨናነቅ የነበረበት ጥበቃ ሲደረግ የአይን እማኞች ገልፀው በተለይም ከአራት ኪሎ ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ መስቀል አደባባይ ድረስ የነበረው ጎዳና ምንም ዓይነት መኪና መቆም እንዳይችል ተከልክሎ ለየት ያለ እንቅስቃሴ ያሳየ ማንኛውም አሽከርካሪ በቁጥጥር ስር ውሎ ፍተሻ እየተደረገበት እንደነበረም ዘገባው አስረድቶዋል።

ያልሰሩትን ሰራን ፣ያላደረጉትን አደረግን እያሉ በባዶ ሜዳ ጉራቸውን የሚያናፍሱት እነ መለስ ዜናዊ ከሱማሊያ ምድር መነሻ ያደረገውን አልሻባብ ጥቃት ሊያደርስብን በመሆኑ አግዙን በማለት ጥሪ ያቀረበ ቢሆንም ህዝቡ ትኩረት እንዳልሰጠው ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሱን ዘገባዎች አስረድተዋል።

የወያኔ ፌዴራል ፖሊስን ጥሪ ተከትሎ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ባወጣው መግለጫ ማንኛውም የአሜሪካ ዜጋ ህዝብ በተሰበሰበበት መዝናኛ ቦታዎች እንዳይገኙ አጥብቆ የከለከለ መሆኑም ታውቆዋል።

በውሸት ላይ የተመሰረተው የወያኔ ቡድን የአልሸባብ ተዋጊ ኃይል ከነ ሙሉ ትጥቁ አዲስ አበባ ገብቶዋል በማለት ቢለፍፍም የወያኔ ባህሪ ውሸት በመሆኑ እራሱ የፈጠረው ታሪክ ሊሆን ስለሚችል እና ሊያስር ያሰበው ኃይል ሲኖር ከዚህ በፊት እንዳደረገው አሁንም በተመሳሳይ እርምጃ ሊወስድ አስቦ ያደረገው ሳይሆን እንዳልቀረ ህዝቡ የወያኔን ጥሪ በጥርጣሬ እያየው መሆኑ ታውቆዋል።

ይህንኑ ተከትሎ ዐርብ እለት ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ. ም. የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ ባስተላለፈው መግለጫ «ከኦነግ ጋር በምስጢር ሲሰሩ የነበሩ የኦፌዴን አባሎችና አመራሮች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራቸው እየተጣራ ይገኛል » በማለት የገለፀ ሲሆን የኦፌዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በበኩላቸው በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ የተገለፀው ሁሉ ውሸትና የፈጠራ ከመሆኑም በላይ የፓርቲውን ስምና ዝና ለማጉደፍና በህዝብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ለማሳጣት ነው በማለት ከረር ያለ መልስ በይፋ ሰጥተዋል።

የወያኔ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ የተባለው ክፍል በበኩሉ የመከላከያ ሰራዊቱ ከአካባቢው ህዝብ ጋር በመተባበር « በምዕራብ ወለጋ ውስጥ ሲንቀሳቀስ የነበረውን አሸባሪውን የኦነግ ክንፍ ደምስሶ በርካቶችን በቁጥጥር ስር ያዋለ መሆኑን ገልፆዋል።

አክሎም በዚሁ በቄለም ወረዳ ውስጥ ሲንቀሳቀስ የነበረውን የኦነግ ክንፍ ሲመራ የነበረው ማዕከላዊ ኮሚቴ እና የጦሩ አዛዥ የነበረው ለገሰ ወጊ የተባለው የኦነግ አመራር በአካባቢው አርሶ አደሮች መገደሉንም ጨምሮ ገልፆዋል።

ጭንቀት ውስጥ የገባው የወያኔው ቡድን በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አንዴ አልሸባብ ጥቃት ሊያደርስ አዲስ አበባ ገባ ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ኦነግና ሻዕቢያ ጥቃት ሊያደርሱ ነበር፤ እንደገና ደግሞ በወለጋ ውስጥ የኦነግን አመራር ገድዬ በርካቶችን ማረኩኝ በማለት በአንድ ጊዜ ሊሆንና ሊገጣጠም የማይችል ነገሮችን መለፈፉ ሊሰራ ያሰበው ድራማ መኖሩ አስቀድሞ የታወቀ በመሆኑ ሊገርመን አይችልም ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሲገልፁ ተደምጠዋል።

በቅርቡ የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው አብዱላሂ የተባለው የወያኔ ካድሬ እራሱን የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ብሎ ከሚጠራው መሪዎች ጋር ግንኙነት አለህ በሚል ከስልጣኑ የተባረረ ከመሆኑም በላይ አዲስ አበባ አስመጥተው የቁም እስረኛ ያደረጉት ሲሆን ፤ በዚህም የተነሳ በክልሉ ባለስልጣናት ዘንድ መረጋጋት ጠፍቶ ብዙ የክልሉ ሹማምንቶች በገዛ ፈቃዳቸው ሲለቁ ሌሎችም ከስልጣናቸው ተባርረው በጅጂጋ ከተማ የቁም እስረኛ እንደነበሩ በወቅቱ መዘገቡ አይዘነጋም።

ኦብነግ ከአልሸባብ ጋር እጅና ጉዋንት ሆነው በኦጋዴን ውስጥ ጥቃት እየፈፀሙ መሆኑን በተደጋጋሚ የገለፀው ወያኔ ሰሞኑንም በጎዴና በቀላፎ አካባቢ በጥበቃ ላይ ባለ የወያኔ ጦር ላይ ድንገተኛ ጥቃት አድርሰው ከ25 ወታደሮች በላይ ገድለው በርካታ ማቁሰላቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል።

ባለፈው ሳምንት ወያኔ በአዲስ አበባ ውስጥ ጥቃት ሊሰነዘርብኝ ነው እያለ በሚወተውትበት ወቅት በጎዴና በቀላፎ 7 መኮንኖችን ጨምሮ 25 ወታደሮችን ገድለው ቁጥራቸው ብዙ የሆኑትን ማቁሰላቸውና ቁስለኞቹም በሂሊኮፕተር ተጉዋጉዘው በሀረር ከተማ ቀላድ አምባ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው የጦሩ ሆስፒታል ውስጥ እና በአዲስ አበባ የጦር ኃይሎች ሆስፒታል ተኝተው ህክምና እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል።

በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ እና በክልል ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ የአልሸባብ አጥፍቶ ጠፊዎች በመንግስታዊ ተቋማትና ባለስልጣናት ላይ ጥቃት ሊሰነዝሩ ይችላል በሚል የተጀመረው ዘመቻ ተቀጣጥሎ በተለይም የአይናቸው ቀለም አላማረንም የተባሉ የኦሮሞ ነጋዴዎች ከዚሁ ጋር ከየቤታቸው እየታፈሱ ወደ እስር ቤት እየተጋዙ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በአሁኑ ሰዓት በማዕከላዊ ምርመራ እስረኞች ከሙብዛ ቸው የተነሳ መጣበቡንም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።

በዚሁ ወያኔ በጀመረው የማስመሰያ ዘመቻ የምዕራብ ሀገር አለቆቹን ድጋፍ ለማግኘት ሲል በተጠናከረ ሁኔታ የአጥፍቶ ጠፊዎችን እያደንኩን ነው እያለ በመወትወት ሲሆን የያዝኩዋቸውን አጥፍቶ ጠፊዎችና ተባባሪዎቻቸውን ለህዝብ እይታ አበቃለሁ የተሰማ ሲሆን፤በአሁኑ ወቅት ወያኔ በፈጠረው ግርግር ህዝቡና ዲፕሎማቶች ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ የገቡ መሆኑንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል።

በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ ሌላው አቢይ ክስተት ሆኖ የነበረው የበላችው ያገሳታል በላይ በላዩ ያገርሳታል እንዲሉ የወያኔ ቡድን በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ምክንያት የሚኒስትሮች ሹም ሽር ከማድረጉም በተጨማሪ የቤንሻንጉል ክልል ፕሬዝዳንት የነበረውን ያረጋል አይሸሹም የተባለውን የወያኔ ከፍተኛ ካድሬ ከስልጣኑ ማባረራቸው ነው::

ያረጋል አይሸሹም የተባለው የቤንሻንጉል ፕሬዝዳንት ለ14 ዓመታት ሲመራው የነበረውን ክልል በፍላጎቱ ለቀቀ ተብሎ ሌላ ካድሬ የተተካ መሆኑ በወያኔ በኩል ቢገለጽም ከአሶሳ የደረሰን ዘገባ ግን ይህ ፍፁም ሀሰት መሆኑን ያስረዳል::

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ አንድ ተጠናክሮ የሚንቀሳቀስ ኃይል እንዳለና ይህ ተዋጊ ቡድን በወያኔ ጦር ላይ ያልታሰበ ጥቃት እንደሚሰነዝርና በክልሉ ባለስልጣናት ላይ ግድያ በመፈፀሙ ከመሀል ሀገር የሄዱ ባለስልጣናትና የመንግስት ሰራተኞች ተረጋግተው ስራቸውን መስራት ባለመቻላቸው የተነሳ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በያረጋል ላይ ጥርጣሬ ከማሳደሩም በተጨማሪ በቅርቡ የአሶሳ ከተማ ከንቲባ የነበረው ካድሬ ብዙ ምስጥሮችን ይዞ ከመሰወሩ ጋር በተያያዘ ከክልል ፕሬዝደንትነቱ የተባረረ መሆኑን ከአሶሳ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

የወያኔ ቡድን ዙሪያ ገባውን በውጥረት ውስጥ ስለወደቀ ብቻ የራሴ ናቸው የሚላቸውን ባለስልጣናት እያባረረ በሌላ ቢተካም ያሰበው ሳይሳካ እንደገና ሌላ ችግር እየተደራረበበት መምጣቱን አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ሲገልፁ ተደምጠዋል::

የገዛ እራሱን ማመን እያቃተው የመጣው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቀድሞ ሲያወድሳቸው የነበሩትን እያራቀ ሲያወግዛቸው የነበሩትን ደግሞ እያቀረበ መምጣቱ ሰውዬው ከፍተኛ የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ መሆኑን ያሳያል ያሉት እኚሁ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር በቅርቡ በተደረገው የሚኒስትሮች ሹም ሽር መፍትሄ ያመጣል ብሎ አስቦ ያደረገ ቢሆንም ነገሮች ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ በመውጣታቸው የተነሳ ግራ ተጋብቶ ከጎኑ አርቆት የነበረውን በረከት ስምኦንን መልሶ በማቅረብ እንደቀድሞው ሁሉ እያቦካ ሲያጨማልቀው እያየ መወሰን ተቸግሮ ከአማኑኤል ሆስፒታል እንደ ወጣ የአዕምሮ ህመምተኛ ባዶ ቢሮ ቆልፎ ብቻውን መቀመጥ ላይ መድረሱን እኚሁ መምህር ጨምረው ገልፀዋል::

በሌላ ዜና ሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ. ም. ከሰዓት በሁዋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስር እንዲገባ በተደረገው የኮሜርስ ኮሌጅ ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ተቀስቅሶ እንደነበር ታወቀ::

በኮሜርስ ግቢ ውስጥ የሚማሩት የዚሁ ኮሌጅ መደበኛ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ሲከፈል የነበረው ገንዘብ ከወቅቱ የኑሮ ሁኔታ ጋር ፍፁም የማይመጣጠን በመሆኑ ይጨመርልን ብለው የተማሪ ተወካዮችን ልከው የኮሌጁን አስተዳደር ቢያናግሩም «መንግስት ከሚችለው በላይ ማድረግ ስለማይችል ትምህርቱን ማቆም ትችላላችሁ» በማለት ምላሽ በመስጠታቸው ተማሪዎቹ ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማታቸው ታውቆዋል::

ከዚህ ቀደም አምና በተመሳሳይ ሁኔታ ጥያቄ አቅርበው የነበረ ቢሆንም አጥጋቢ ምላሽ ያላገኙት ተማሪዎቹ ዘንድሮ ችግሩ ስለጠናባቸው ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርቡም የንቀት መልስ ከወያኔ ካድሬው አስተዳደር የተሰጣቸው በመሆኑ ተቃውሞአቸውን በግቢያቸው ውስጥ በማሰማት ላይ እንዳሉ የእውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን የውሳኔ ቀጠሮ መራዘሙን በመስማታቸው ተቃውሞው ይበልጥ እየተቀጣጠለ በመሄዱና

በአካባቢው ሲንቀሳቀስ የነበረውንም ህዝብ ጭምር ቀልብ በመሳባቸው የፌዴራል ፖሊስ እግቢ ውስጥ ድረስ ዘልቆ ገብቶ ተማሪዎቹን ደብድቦ በርካቶችን አፍሶ ወዳልታወቀ ቦታ ከመውሰዱም በተጨማሪ የተማሪዎቹን መማሪያ ክፍል መስታወቶች በመሰባበር ከጥቅም ውጭ ያደረገ መሆኑም ተማሪዎቹ ገልፀዋል::

የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ ይህንን የግፍ እርምጃ በተማሪዎቹ ላይ መውሰዱን ተከትሎ የደህንነት ሰራተኞች በግቢው ውስጥ በመግባት ሴት ተማሪዎችን በአንድ ክፍል ውስጥ ሰብስበው አስገብተው የደበደቡዋቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ከዚህ በሁዋላ አስተዳደሩ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝና መመሪያ ብቻ እንዲቀበሉ በማስጠንቀቂያ እንደለቀቁዋቸው ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ሳይጠሩዋቸው አቤት ሳይልኩዋቸው ወዴት የሚሉት ቅልብ የወያኔ ፌዴራል ፖሊሶች እዚያው ለገሀር አካባቢ የቀድሞው ጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ሰፍረው ስላሉ ከግቢያቸው ወጥተው ዙሪያውን ኮሌጁን ከብበው አንድም ተማሪ ወደውጭ እንዳይወጣ አድርገው የደበደቡዋቸው መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ተማሪዎቹ ያነሱት የመብት ጥያቄ መሆኑን እንኩዋን ያልተረዱ የጋሪ ፈረሶች መሆናቸውን የሳየ ነው ሲሉ በግቢው ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራኖች በአግራሞት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ከአዲስ አበባ ለተመደበ ተማሪ በወር 240 ብር ከክፍለ ሀገር ለተመደበ ደግሞ 300 ብር የሚሰጣቸው ቢሆንም አሁን ባለው ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ ጋር ፍፁም ሊጣጣምላቸው ስላልቻለ የማደሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ጭምር ቢጠይቁም የትምህርት ቤቱ የወያኔ ካድሬ አስተዳደሮች በጎ ምላሽ ሳይሰጡዋቸው ዛሬም እያጉላሉዋቸው መሆኑን የገለፁት ተማሪዎቹ ሲብስባቸው ተቃውሞውን እንዳሰሙና አሁንም ተገቢ ምላሽ ካላገኙ ተቃውሞ ማሰማታቸውን እንደሚቀጥሉበት አስረድተዋል::

አንዳንድ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች እንደሚገልፁት ከሆነ ከክፍለ ሀገር መጥተው የሚማሩት ተማሪዎች በሚሰጣቸው ገንዘብ ወር ሙሉ ሊያቆያቸው ቀርቶ 15 ቀን የማያደርሳቸው በመሆኑ በየዓመቱ ከቤተሰብ ተገዝቶ የሚሰጣቸውን ልብስ እስከ መሸጥ የደረሱ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ማደሪያ ከመቸገራቸው የተነሳ በመርካቶ ውስጥ በሚገኙ በግማሽ ጎን መኝታ ቤቶች በቀን አንድ ብር እየከፈሉ ለመኖር እንደተገደዱ እና ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመማር እንደተቸገሩ ገልፀዋል::

በቀን አንድ ጊዜ መጠኑ ያነሰ ዳቦ ከውሀ ጋር እየቀመሱ እንደሚማሩ የገለፁት ተማሪዎቹ ይህንን ችግር ሁሉ ተጋፍጠው እንዳሉ ቢያስረዱም አድማጭ እና ተመልካች በማጣታቸው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተቃውሞ ቢያሰሙም በፌዴራል ፖሊስ ለመደብደብ እንደበቁ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ. ም. የእውቁ አርቲስት ቴዎድሮስ ካሣሁን የውሳኔ ቀን በመሆኑ እና ህዝብ በጉጉት ሲጠባበቅ ቢቆይም በ7 ደቂቃ ውስጥ ችሎቱ በሌላ ቀጠሮ ሊበተን እንደቻለ የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ሰኞ ዕለት ከሰዓት በሁዋላ ለውሳኔ የተቀጠረውን የቴዲ ውጤት ለመከታተል ከጠዋቱ 4 ሰዓት ጀምሮ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውስጥ አድናቂዎቹ፤ የሙያ ባልደረቦቹና ዘመድ አዝማዶቹ የተገኙ ሲሆን በግቢው ውስጥ ቆይተው ቦታ ለመያዝ ቢሞክሩም የፌዴራል ፖሊሶች ዱፍ ዝናብ እየዘነበ ከግቢ እንዲወጡ ያደረጋቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ ይህንን ሁሉ ችግር ተጋፍጠው ጥቂት የገቡ ቢኖሩም የወያኔው ካድሬ ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም በ7 ደቂቃ ውስጥ ችሎቱን ለመበተን እንደቻለ ገልፆዋል::

እብሪተኛው ፤ ማን አለብኝ የሚለው፤ ሙሰኛውና ሴሰኛው የወያኔ ካድሬ ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ለቲዲ ባለው ውስጣዊ ጥላቻ የተነሳ አንዴም ቀና ብሎ ሳያይ « ውሳኔ ስላልተሰራ ለህዳር 22 ቀን 2001 ዓ. ም. » በማለት ቀጠሮ የሰጠ ሲሆን አዲሱ የቲዲ ጠበቃ ቀጠሮው አይረዝምም ወይ? ብለው ሲጠይቁ « የማያዳግም እርምጃ ለመስጠት ነው» በማለት ፋይሉን እየወረወረ እብሪትና ትዕቢት የተቀላቀለበት ምላሽ ሰጥቶ በፍርድ ቤት ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ 7 ሰዓት ከ55 ደቂቃ ችሎቱ ተሰይሞ 8 ሰዓት ከ02 ደቂቃ በ7 ደቂቃ ውስጥ ችሎቱን እንደጨረሰ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ከመጀመሪያውም አንስቶ ቲዲ በሌለበትና ባልሰራው ወንጀል ሆን ተብሎ በተቀነባበረና ሀሰተኛ በሆነ ሁኔታ ተከስሶ ከ6 ወራት በላይ ለእስር የተዳረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የተከሰሰበትን ክስ ከበቂ በላይ በማስረጃ በማስደገፍ በመከላከሉ ነፃ ወጥቶ ስማችንን ያጠፋዋል ብለው የወያኔ ሹማምንቶች በመስጋታቸው አረመኔው ዳኛ ልዑል ከተነሳበት ችሎት እንደገና እንዲመለስ አድርገው ያመጡት ሲሆን የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም እንዲሉ እሱም የማያዳግም እርምጃ እሰጣለሁ በማለቱ በችሎቱ ውስጥ የተገኙት አድናቂዎቹና ቤተሰቦቹ ዘንድ ድንጋጤን በመፍጠሩ ሲላቀሱ እንደነበር ዘገባው አብራርቶዋል::

በዕለቱ ወደ ችሎት ለመግባት በግቢው ውስጥ ከነበሩት የሙያ ባልደረባዎቹ ውስጥ ጥበቡ ወርቅዬ የነበረ ሲሆን ድምፃዊ ጥበቡ ወርቅዬን የወያኔ ደህንት ካሜራ ማን የሆነው ግለሰብ እየተዘዋዘዋረ ሲቀርፀው ለምን ከኔ ፍላጎትና ፍቃድ ውጭ ትቀርፀኛለህ በሚል በተፈጠረው ፀብ ድምፃዊ ጥበቡን ለሰዓታት እዚያው ግቢ ውስጥ የፌዴራል ፖሊሶች አግተውት እንዳቆዩት እና እንደለቀቁት ከዓይን እማኞች ለመረዳት ተችሎዋል::

በተያያዘ የእውቁ ድምፃዊ የቲዎድሮስ ካሣሁን ዳኛ ተቀየሩ በሚል ርዕስ የአባት ስም ተሳስታለች ተብላ ታስራ የነበረችው የእንቢልታ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ወ/ሮ ፅዮን ግርማ የሁለት ሺህ ብር ቅጣት እንደተጣለባት ታወቀ::

በአረመኔው «ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ምትክ የቅንጅት አመራሮችን የክስ ሂደት ሲከታተሉት የነበሩት የግራ ዳኛ መሐመድ ዑመር መሾማቸው ታውቆዋል» ብላ በጋዜጣ ላይ በማሳተሙዋ ብቻ የሁለት ሺህ ብር መቀጮ የተጣለባት ሲሆን መሐመድ ዑመር የተባለው መሀመድ ሳኒ መሆኑን ይቅርታ ጠይቃ ብታትምም ውስጣቸው በመርዝ የተለወሰው የወያኔ ጀሌ ካድሬ ዳኞች ውሳኔ ከመስጠት እንዳልተመለሱ ከወሰዱት እርምጃ ታውቆዋል::

ከቢሮዋ በድንገት ተይዛ ለእስር የተዳረገችው የእንቢልታ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በተደጋጋሚ ጊዜ የቲዲን ጉዳይ እየተከታተለች በመዘገብዋ እና በስልክ ማሳፈራሪያ ቢሰጣትም በአቋዋሙዋ በመፅናትዋ ቅጣቱ እንደተጣለባት ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል::